# የገንዘብ ሚኒስቴር

## የታክስ ከፋይ ምዝገባ እና ሥረዛ የአፈጻጸም

## መመሪያ ቁጥር 3/2011

ገንዘብ ሚኒስቴር

መጋቢት 2011 ዓ.ም

Ministry of
ARCHIVES
2
Finance

# የታክስ ከፋይ ምዝገባ እና ሥረዛ የአፈጻጸም
# መመሪያ ቁጥር 3/2011

## 1. <u>አውጪው ባለሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 136 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በታክስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 407/2009 አንቀጽ 20 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

## 2. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የታክስ ከፋይ ምዝገባ እና ሥረዛ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 3/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. <u>ትርጓሜ</u>

በታክስ አስተዳደር አዋጅ ትርጉም የተሰጠው ቃል ወይም ሀረግ በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ በአዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

ሀ) "የታክስ ከፋይ ምዝገባ" ማለት በታክስ ህግ መሰረት ታክስ የመክፈል ኃላፊነት ያለበትን ሰው በፀደቀው ቅጽ መሰረት በመመዝገብ የምስክር ወረቀት መስጠት ነው፡፡

ለ) "የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር" ማለት በታክስ ከፋይነት የተመዘገበ ሰው ለታክስ ህጎች ዓላማ ሲባል ተለይቶ የሚታወቅበት በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ቁጥር ሲሆን፣ የፌደራል መንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ለይቶ ለማወቅ የሚሰጠውን ቁጥር ይጨምራል፡፡

ሐ) "ተቀጽላ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር" ማለት ከአንድ በላይ ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ውስጥ በንግድ ሥራ ወይም ቤት በማከራየት ገቢ ለሚያገኝ ግለሰብ ወይም ድርጅት በስሙ ከተመዘገበው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር በኋላ ወይም በፊት የሚቀመጠው ተቀጽላ ቁጥር ወይም ፊደል ወይም ሰረዝ ነው፡፡

Ministry of Finance ARCHIVES 2

መ) "የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ" ማለት በንግድ ሥራ ላይ ለመሰማራት አግባብ ባለው ፈቃድ ሰጪ ባለስልጣን የሚሰጥ የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም በየጊዜው የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ነው፡፡

ሠ) "የማንነት አካላዊ መረጃ" ማለት የግለሰቡን ማንነት ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ የሚውል የግለሰብ ማንነት መለያ አካላዊ መረጃ ማለትም የፊት ገጽታ መለያ፣ የጣት አሻራ መለያ፣ የድምጽ መለያ ወይም የዓይን ክፍሎች (ምጣኔ ብርሃን ወይም መቅረፀ ምስል) መለያ ነው፡፡

ረ) "የንግድ ማህበር" ማለት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ የአክሲዮን ማህበር እና የሽርክና ማህበር ሲሆን፣ በንግድ ሥራ የተሠማራን ማናቸውም ሌላ ማህበር ይጨምራል

ሰ) "ባለሥልጣን" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬዳዋ አስተዳደር ገቢዎች ባለሥልጣን ነው፡፡

ሸ) "አዋጅ" ማለት የፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው፡፡

ቀ) "ደንብ" ማለት የፌዴራል የታክስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 407/2009 ነው፡፡

4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአዋጁ መሰረት ለታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ ባለበት ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ለታክስ ከፋይነት ስለመመዝገብ

5. <u>ለታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ ያለባቸው ሰዎች</u>

1. ለአዋጁ አንቀጽ 9 አፈፃፀም አስቀድሞ የተመዘገበ ካልሆነ በስተቀር ታክስ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ሰው በባለስልጣኑ ዘንድ የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡

   ሀ) በንግድ ወይም በሙያ ሥራ (መቀጠርን ሳይጨምር) የተሰማራ ግለሰብ
   ለ) ቤት በማከራየት ገቢ የሚያገኝ ግለሰብ

MINISTRY OF ARCHIVES 2 Finance

ሐ) ተቀጣሪ
መ) የንግድ ማህበር
ሠ) የመንግስት የልማት ድርጅት
ረ) የመንግስት ባለበጀት መ/ቤት
ሰ) መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅቶች
ሸ) የሃይማኖት ተቋማት
ቀ) በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ኩባንያ በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት፣
በ) የፌደራል መንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች
ተ) በጋራ ሀብትነት ያልተመዘገበ ሀብት ያላቸው ሰዎች
ቸ) ባለ ልዩ መብት
ኀ) በመንግሥታት መካከል በሚደረግ ስምምነት ወይም በጽ/ቤት ማቋቋሚያ ስምምነት የሚቋቋሙ ድርጅቶች፣
ነ) የኩባንያ አክሲዮን ባለድርሻ፣

2. በአዋጁ አንቀጽ 9 በተደነገገው መሠረት ለታክስ ከፋይነት መመዝገብ ያለበት ሰው እንደሁኔታው ሥራውን ከመጀመሩ ወይም ገቢ ከማግኘቱ በፊት ለታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ የምዝገባ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡

## 6. ለታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

1 በንግድ ወይም በሙያ ሥራ (መቀጠርን ሳይጨምር) የተሰማራ ወይም ቤት በማከራየት ገቢ የሚያገኝ ግለሰብ እንዲሁም ተቀጣሪ በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ ሲቀርብ

ሀ) በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ማቅረብና የማንነት አካላዊ መረጃ መስጠት፣

ለ) ወቅታዊ ወይም የታደሰ የግለሰቡ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም የግለሰቡን የግል መረጃ የያዘ ወቅታዊ የኢትዮጵያ ወይም የሌላ አገር ፓስፖርት ወይም የግለሰቡን የግል መረጃ የያዘ፣ ጉርድ ፎቶግራፍ የተለጠፈበት ወቅታዊ የኢትዮጵያ ወይም የሌላ ሀገር የታደሰ መንጃ ፈቃድ፣

ሐ) አመልካቹ ታክስ ከፋይ ከስድስት ወር ወዲህ የተነሳው ጉርድ ፎቶግራፍ እና

መ) አመልካቹ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ሞግዚት ከሆነ ይህንን የሚያረጋግጥ ከፍርድ ቤት የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

Ministry of Finance ARCHIVES 2

ሠ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ ከሀ እስከ መ ላይ የተዘረዘሩ ማስረጃዎችን ማቅረብ እንደተጠበቀ ሆኖ ቤት በማከራየት ገቢ የሚያገኝ ግለሰብ የቤቱ ባለቤት ከሆነ የቤቱን ካርታ ወይም የተከራይ አከራይ ከሆነ ቤቱን የተከራየበትን ውል ማቅረብ ይኖርበታል፡

ረ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 በፊደል ተራ ቁጥር ከሀ እስከ ሐ ላይ የተዘረዘሩ ማስረጃዎችን ማቅረብ እንደተጠበቀ ሆኖ ተቀጣሪ በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ የቅጥር ውል ወይም ደብዳቤ፤ የቀጣሪውን ስምና አድራሻ የሚገልጽ የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል።

2. የንግድ ማህበር በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ በሚቀርብበት ጊዜ፣

ሀ) በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውንና በሚገባ የተሞላውን የማመልከቻ ቅጽ፣

ለ) በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ የማህበር መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ፣

ሐ) የድርጅቱ ጽ/ቤት (የስራ ቦታ) በማህበሩ ባለቤትነት ሥር ያለ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ከሆነ በውልና ማስረጃ የፀደቀ ውል፣

መ) የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም የታደሰ መንጃ ፈቃድ፣ ከስድስትወር ወዲህ የተነሳው ጉርድ ፎቶግራፍ እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣

ሠ) አመልካቹ ወኪል ከሆነ ስለውክልናው የተሰጠውን ህጋዊ የውክልና ማስረጃ ወይም በምስረታ ላይ ላለ ማህበር ወኪል ለመሆን በሁሉም አባላትፊርማ የተረጋገጠ ውክልና

ረ) ከማህበርተኞቹ መካከል የውጭ ሀገር ዜጋ ካለ ማንነቱን የሚገልጽ ፓስፖርት ኦርጅናልና ፎቶ ኮፒ እንዲሁም ከኢንቨስትመንት ጽ/ቤት የተሰጠ ማስረጃ፣ ማቅረብ ይኖርበታል።

ሰ) የእሽሙር ማኅበርን በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ለ የተጠቀሰው መስፈርት ተፈጻሚ አይሆንም ።

3. የመንግስት የልማት ድርጅቶች በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ በሚቀርቡበት ጊዜ፡-

ሀ) በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውንና በሚገባ የተሞላውን ቅጽ፣

Ministry of ARCHIVES 2 Finance

ለ) ድርጅቱ የተቋቋመበት ህግ ፣
ሐ) የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የምደባ ደብዳቤ፣
መ) ወቅታዊ ወይም የታደሰ የሥራ አስኪያጁ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም የሥራ አስኪያጁን የግል መረጃ የያዘ ወቅታዊ የኢትዮጵያ ወይም የሌላ አገር ፓስፖርት ወይም የሥራ አስኪያጁን የግል መረጃ የያዘ ፎቶግራፍ የተለጠፈበት ወቅታዊ የኢትዮጵያ ወይም የሌላ ሀገር የታደሰ የመንጃ ፈቃድ፣
ሠ) የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ከስድስት ወር ወዲህ የተነሳው ጉርድ ፎቶግራፍ እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ፣
ረ) አመልካቹ ወኪል ከሆነ ስለውክልናው የተሰጠውን ህጋዊ የውክልና ማስረጃ፣

4. የመንግስት ባለበጀት መ/ቤት በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ በሚቀርብበት

ሀ) በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውንና በሚገባ የተሞላውን ቅጽ፣
ለ) የመ/ቤቱ ማቋቋሚያ ህግ፣
ሐ) መ/ቤቱን የሚወክለው ሰው የውክልና ደብዳቤና የግለሰቡ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር

5. መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ በሚቀርቡበት ጊዜ፣

ሀ) በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውንና በአግባቡ የተሞላውን ቅጽ፣
ለ) በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ፣
ሐ) የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የምደባ ደብዳቤ፣
መ) የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም የሥራ አሥኪያጁን የግል መረጃ የያዘ ፎቶግራፍ የተለጠፈበት የመንጃ ፈቃድ እንዲሁም ከስድስት ወር ወዲህ የተነሳው ጉርድ ፎቶግራፍ እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣

6. የሃይማኖት ተቋማት በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ በሚቀርቡበት ጊዜ፣

ሀ) በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውንና በአግባቡ የተሞላውን ቅጽ፣
ለ) አግባብ ካለው የመንግስት አካል የተሰጠ የምዝገባ የምስክር ወረቀት፣
ሐ) የሃይማኖት ተቋሙን የሚወክለውን ሰው ሕጋዊ የውክልና ማስረጃ፣
መ) የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ወይም ተወካይ ከስድስት ወር ወዲህ የተነሳው ጉርድ ፎቶግራፍ እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣

Ministry of ARCHIVES 2 Finance

7. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ኩባንያ በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ በሚቀርብበት ጊዜ፣

ሀ) በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውንና በአግባቡ የተሞላውን ቅጽ፣

ለ ) በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ኩባንያ በውጪ ሀገር የተመሰረተበትን የምስክር ወረቀት፣

ሐ) በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው ኩባንያ በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት የሚሰራበትን ቦታ አድራሻ የሚገልጽ ሰነድ

መ) የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ከስድስት ወር ወዲህ የተነሳው ጉርድ ፎቶግራፍ እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ፣

ሠ) አመልካቹ ወኪል ከሆነ የተሰጠውን ህጋዊ የውክልና ማስረጃ፣

8. የፌደራል መንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች (ተማሪዎች) ለመመዝገብ በሚቀርቡበት ጊዜ፣

ሀ) በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውንና በአግባቡ የተሞላውን ቅጽ፣

ለ) የማንነት አካላዊ መረጃ መስጠት፣

ሐ) በሚማርበት የዩኒቨርስቲ የታደሰ መታወቂያ ካርድ፣

9. በጋራ ሀብትነት ያልተመዘገበ ሀብት ያላቸው ሰዎች እንዲሁም ባለ ልዩ መብቶች በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ በሚቀርቡበት ጊዜ፣

ሀ) በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ፣

ለ) የማንነት አካላዊ መረጃ መስጠት፣

ሐ) ወቅታዊ ወይም የታደሰ የግለሰቡ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም የግለሰቡን የግል መረጃ የያዘ ወቅታዊ የኢትዮጵያ ወይም የሌላ አገር ፓስፖርት ወይም የግለሰቡን የግል መረጃ የያዘ፣ ጉርድ ፎቶግራፍ የተለጠፈበት ወቅታዊ የኢትዮጵያ ወይም የሌላ ሀገር መንጃ ፈቃድ ወይም የግለሰቡ የተረጋገጠ የልደት የምስክርወረቀት፣

መ) አመልካቹ ታክስ ከፋይ ከስድስት ወር ወዲህ የተነሳው ጉርድ ፎቶግራፍ እና

Ministry of ARCHIVES 2 Finance

ሠ) የጋራ ሀብቱ ባለቤቶች በውልና ማስረጃ የተረጋገጠ ሙሉ ውክልና የሰጡበት የሰነድ ማስረጃ

ረ) በዚህ አንቀጽ በፊደል ተራ ከሀ እስከ ሐ ላይ የተዘረዘሩ ማስረጃዎችን ማቅረብ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለልዩ መብት ልዩ መብት ያለው ስለመሆኑ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

10. በመንግሥታት መካከል በሚደረግ ስምምነት ወይም በጽ/ቤት ማቋቋሚያ ስምምነት የተቋቋሙ ድርጅቶች ለምዝገባ በሚቀርቡበት ጊዜ፣

ሀ) ድርጅቱ ወይም ጽ/ቤቱ የተቋቋመበት ስምምነት፣

ለ) የድርጅቱ ወይም የጽ/ቤቱ ሥራ አሥኪያጅ የምደባ ደብዳቤ፣

ሐ) የሥራ አሥኪያጁ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

መ) የሥራ አሥኪያጁ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም የኢትዮጵያ ወይም የሌላ ሀገር ፓስፖርት፣ ወይም የኢትዮጵያ ወይም የሌላ ሀገር የመንጃ ፈቃድ፣

ሠ) የፓስፖርት መጠን ያለው ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣

## 7. <u>የምዝገባ ቦታ</u>

1. የታክስ ከፋይነት ምዝገባ የሚከናወነው እንደ አግባብነቱ ታክስ ከፋይ ነዋሪ በሆነበት ወይም የንግድ ሥራውን በሚያከናውንበት ሥፍራ ባለው የታክስ ባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ነው፡፡

2. በባለሥልጣኑ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም ህጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት በታክስ ከፋይነት መመዝገብ ያለበት ዋና መስሪያ ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ የታክሱ ባለሥልጣን ባለው ቅ/ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

3. ከአንድ በላይ በሆነ ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ውስጥ በንግድ ስራ የተሰማራ ወይም ቤት በማከራየት ገቢ የሚያገኝ ግለሰብ ወይም ድርጅት ገቢውን በአገኘበት በእያንዳንዱ ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር መመዝገብ አለበት፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ውስጥ በተለያየ ቦታ የንግድ ሥራ የሚያካሄድ ወይም ቤት በማከራየት ገቢ የሚያገኝ ግለሰብ በታክስ ከፋይነት መመዝገብ ያለበት ዋና መሥሪያ ቤቱ በሚገኝበት ቦታ ባለው የታክሱ ባለሥልጣን ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ይሆናል፡፡

Ministry of Finance ARCHIVES 2

5. ታክስ ከፋይ በተለያዩ ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ በአንድ ወይም በተለያዩ የንግድ ዘርፎች ላይ የተሠማራ ከሆነ በምዝገባ ማመልከቻ ቅጹ ላይ የሁሉንም አድራሻ እና የንግድ ዓይነት ዝርዝር መሙላት አለበት፡፡

## 8. የታክስ ከፋይ ምዝገባ ልዩ ሁኔታዎች

1. አመልካቹ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ሞግዚት በሚሆንበት ጊዜ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ የማንነት አካላዊ መረጃ እንዲሰጥ በማድረግ በስሙ የሚመዘገብ ይሆናል፡፡

2. በሞግዚነት የሚተዳደር ለአቅመ አዳም ያልደረሰ ሰው የማንነት አካላዊ መረጃ በመስጠት በስሙ የሚመዘገብ ቢሆንም የማስተዳደር ኃላፊነቱ ግን የሞግዚቱ ይሆናል፡፡

3. መመዝገብ ሲኖርበት ያልተመዘገበን ሰው ባለሥልጣኑ በፀደቀው ቅጽ መሠረት ሊመዘግብ የሚችል ሲሆን በ አስር ቀናት ውስጥም ታክስ ከፋዩ በአካል ቀርቦ እንዲመዘገብ በደብዳቤ ጥሪ ሊያደረግለት ይችላል፡፡

4. ባለሥልጣኑ የኤሌክትሮኒክስ የታክስ ሥርዓት ተግባራዊ ሲያደርግ ታክስ ከፋዩ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ሊመዘገብ ይችላል፡፡

5. በሠንጠረዥ "መ" መሠረት የመጨረሻ ታክስ የመክፈል ግዴታ የተጣለበት ታክስ ከፋይ ይህንን ገቢ በማመለከት በታክስ ከፋይነት ሊመዘገብ አይችልም፡፡

6. በውጪ ሀገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ሰው ለታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ በአካባቢው በሚገኝ የኢትዮጵያ ኢምባሲ ወይም ቆንስላ በአካል በመገኘት የማንነት አካላዊ መረጃ መስጠት ይችላል፡፡

## 9. የታክስ ከፋይነት ምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ

የታክስ ከፋይነት የምዝገባ ምስክር ወረቀት በባለሥልጣኑ ሊሠረዝ የሚችለው በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፡፡

1. ለታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ለሁሉም የታክስ ህጎች የተጣለበት የመመዝገብ ግዴታ ከተቋረጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ወይም ባለስልጣኑ በሚሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ምዝገባው እንዲሰረዝለት ማመልከት አለበት፡፡

Ministry of Finance ARCHIVES 2

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ምዝገባው እንዲሰረዝለት ማመልከቻ ያቀረበ ታክስ ከፋይ በሌላ የታክስ ህግ ለአንድ የተለየ ታክስ የተደረገው ምዝገባ ጭምር እንዲሰረዝለት እንዳመለከተ ተደርጎ ይወሰዳል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ምዝገባ እንዲሰረዝለት ታክስ ከፋዩ ማመልከቻ ሲያቀርብ ባለሥልጣኑ ለኦዲት ሊያቀርብ የሚገባውን ማስረጃ በመዘርዘር በጽሁፍ በማሳወቅ ታክስ ከፋዩ ሥራውን ያቆመ መሆኑንና በሁሉም የታክስ ህጎች የመመዝገብ ግዴታ የሌለበት መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ የጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት በ30 ቀናት ውስጥ ምዝገባውን ይሰርዘዋል።

4. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የታክስ ከፋይነት ምዝገባ ይሰረዝልኝ ማመልከቻው ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በ90 ቀናት ውስጥ የታክስ ከፋዩን የታክስ ጉዳዮች በተመለከተ የመጨረሻ ኦዲት ሊያደርግ ይችላል።

5. የታክስ ከፋዩ ምዝገባ የተሠረዘ ቢሆንም ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 መሰረት ባለሥልጣኑ ባከናወነው ኦዲት መሠረት ወይም ኦዲት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው እና/ወይም የታክስ ኦዲት ካላደረገ ራሱ ባሳወቀው ወይም ቀደም ብለው በተሰጡ ውሳኔዎች መሠረት የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ የመክፈል ግዴታ አለበት።

6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 እና 5 ድንጋጌዎች ቢኖሩም ታክስ ከፋዩ ያቀረበው የታክስ ማስታወቂያ የተጭበረበረ ወይም ከፍተኛ የቸልተኝነት ድርጊት መኖሩ በማንኛውም ጊዜ በሚደረግ ኦዲት ማረጋገጥ የተቻለ እንደሆነ ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን እንዲከፍል ውሣኔ ሊሰጥ ይችላል።

7. በአዋጁ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ማናቸውም ሰው ምዝገባ እንዲሰረዝለት ጥያቄ ያላቀረበ እንደሆነ እና ይህ ሰው በታክስ ሕጐች መሠረት ያለበትን የማስታወቅ ግዴታ ለሦስት ዓመታት ሳይወጣ የቀረ እንደሆነ ሥራውን ሙሉ በሙሉ በማቆሙ ምክንያት ለታክስ ሕጎች ዓላማ የመመዝገብ ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንዲሁም የተፈጥሮ ሰው ከሆነ መሞቱ፣ ኩባንያ ከሆነም መፍረሱን፣ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ህልውናው መቋረጡን ባለሥልጣኑ ሲያረጋግጥ የታክስ ከፋይነት ምዝገባውን ሊሰርዝ ይችላል።

8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 የተመለከተው ቢኖርም በታክስ ከፋዩ ሞት ምክንያት የሥራው እንቅስቃሴ ካልቆመና ወራሽ ወይም ሞግዚት ተተክቶ የሚሰራ ከሆነ ህጋዊ ወራሽነቱን ወይም ሞግዚትነቱን እስኪያረጋግጥና ስም እስኪዞር ድረስ በ12 ወር ወይም በፍርድ ቤት የንብረት አስተዳዳሪ አስወክለው ከመጡ ጉዳዩ እስኪጠናቀቅ ድረስ የታክስ ከፋይነት የምስክር ወረቀት ላይመለስ ይችላል።

Ministry of ARCHIVES 2 Finance

9. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ከተመለከተው በተጨማሪ የታክስ ምዝገባ ሊሠረዝ የሚችልባቸው ሌሎች መስፈርቶች በመመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር

### 10. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ስለመስጠት

1. ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 9 መሠረት ለታክስ ህጎች ዓላማ ሲባል ለ ታክስ ከፋይ አንድ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሚሰጥ ሲሆን አንድ ታክስ ከፋይ ከአንድ የታክስ መለያ ቁጥር በላይ ሊኖረው አይችልም፡፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የሚሰጠው ምዝገባው በሚከናወንበት ጊዜ ይሆናል፡፡

3. በታክስ ከፋይነት የተመዘገበ ሰው የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳያወጣ እና በንግድ ሥራ ላይ ሳይሠማራ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ሠርቲፊኬት በመያዙ ብቻ የታክስ ግዴታ እንዲወጣ ሊጠየቅ አይችልም፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጸና የንግድ ሥራ ፈቃድም ሆነ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ሠርቲፊኬት ባይኖረውም ማንኛውም ገቢ ያገኘ ሰው ታክስ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ወይም የከተማ አስተዳር በንግድ ሥራ ወይም ቤት በማከራየት ሥራ ላይ ተሠማርቶ ገቢ የሚያገኝ ሰው በእያንዳንዱ ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ተቀጽላ ያለው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ሊሰጠው ይችላል፡፡

7. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት በተለያየ ምክንያት ከጠፋና ታክስ ከፋዩ በባለስልጣኑ በተዘጋጀ ቃለ መሀላ ፎርም ሞልቶ ያቀረበ እንደሆነ ነባሩን የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የያዘ የምስክር ወረቀት ታትሞ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡

8. የታክስ ከፋዩ የታክስ መለያ ቁጥር በተለያዩ ምክንያቶች ከተበላሸና በጽሁፍ ካመለከተ የተበላሸወን መልሶ ነባሩን የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የያዘ የምስክር ወረቀት ታትሞ ይሰጠዋል፡፡


ARCHIVES 2

## 11. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር አጠቃቀም

1. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የተሰጠው ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን ለታክስ ዓላማ በባለሥልጣኑ በተዘጋጀ ሰነድ ላይ ሁሉ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የታክስ መለያ ቁጥር የተሰጠው ታክስ ከፋይ ለታክስ ዓላማ በሚያቀርባቸው ሰነዶች ላይ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን የማይገልጽ ከሆነ ባለሥልጣኑ የቀረበውን ሰነድ እውቅና ላይሰጠው ይችላል፡፡

3. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የተሰጠው ሰው ከታክስ ወኪሉ በስተቀር ለሌላ ለማንኛውም ሰው ዋናውን የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት ወይም መታወቂያ አሳልፎ መስጠት አይችልም፡፡

## 12. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ስለሚሰረዝበት ሁኔታ

1. የታክስ አስተዳደር አዋጅና ደንቡን በትክክል ለማስፈፀም በወጣው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 መሠረት ከታክስ ከፋይነት የተሰረዘ ሰው በባለሥልጣኑ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩ እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲሰረዝ የተደረገ ታክስ ከፋይ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9(5) እና (6) መሠረት የሚፈለግበትን ግብር እንዲከፍል በባለሥልጣኑ ሊጠየቅ ይችላል፡፡

3. የተመዘገበው ታክስ ከፋይ እውነተኛ ማንነቱን የማይገልጽ የማንነት ሰነድ ማስረጃ ወይም የማንነት አካላዊ መረጃ ማቅረቡን በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ የታክስ ከፋዩ መለያ ቁጥር ይሰረዛል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ ታክስ ከፋዩ ከአንድ በላይ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር መያዙን ካረጋገጠ በአንዱ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ላይ ያለውን መረጃ እና የታክስ እዳ ሙሉ በሙሉ እውነተኛ ማንነቱን ወደ ሚገልጸው የታክስ ከፋዩ መለያ ቁጥር በማዞርና የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት እንዲሰረዝ ያደርጋል፡፡

5. ታክስ ከፋዩ ማንኛውንም ገቢ የሚያገኝበትን ሥራ ሲያቆም የታክስ ከፋዩን የመለያ ቁጥር የመሰረዝ ኃላፊነት የባለስልጣኑ ይሆናል፡፡

Ministry of ARCHIVES 2 Finance

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌ

13. **የአፈጻጸም ሥርዓት ስለመዘርጋት**

ባለሥልጣኑ ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም የሚረዳ የአሠራር ሥርዓት ሊዘረጋ ይችላል፡፡

14. **የተሻሩ መመሪያዎች**

በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የወጣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 11/2001 እና ሌሎች ይህን መመሪያ የሚቃረኑ አሠራሮች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

15. **የመመሪያው ተፈጻሚነት**

ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 1 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ መጋቢት 20 ቀን 2011 ዓ.ም.*

*አህመድ ሺዴ*
*የገንዘብ ሚኒስትር*